


ፓስተር ቶኒ አላሞ | የአላሞ የክርስትያን ሕዝብ | ቅጽ 17800

# በደህንነት እና በሃይማኖት መካከል ያለ ልዩነት

**በቶኒ አላሞ**



*ቶኒ እና ሱዛን አላሞ፥ ኦርኬስትራ እና መዘምራን በቴሌቭዥን ፕሮግራማቸው ላይ በ 1970ዎቹ እና በ 80ዎቹ መጀመርያ*

ከዳኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ከተወለዱ ሰዎች ይልቅ እጅግ የሚበዙ ሃይማኖተኛ ሰዎች በዚህ አለም ውስጥ አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሃይማኖት ከሰይጣን እንደሆነ፥ ነገር ግን መዳን ከጌታ እንደሆነ በብዙ ቃላት ይነግረናል።[1]

በክርስቶስ በማመን እና በሃይማኖት በማመን መካከል ያለው ልዩነት፥ በክርስቶስ ስናምን ሰውን የሚፈልገው እግዚአብሔር ነው። በሌላ ቋንቋ፥ እግዚአብሔር ነው ሰውን የፈለገው፥ አሁንም የሚፈልገው። እግዚአብሔር ቀድሞ አዳምን፥ ቃየንን፥ ሴትን (ሶስተኛው የአዳም ልጅ)፥ ሄኖክን፥ ኖህን፥ አብርሃምን፥ ይሳቅን እና ያዕቆብን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተገናኘ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እርሱ ቀድሞ ማቴዎስን፥ ዩሐንስን እና ሐዋርያው ጳውሎስን ተገናኘ። በ 1964 እርሱ ከእኔ ጋር ተገናኘ፥ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እና በአሁን መካከል ብዙዎች ነበሩ። በሌላ ቃላት፥ እግዚአብሔር፥ ሁሉንም ዳንግሌ በጎች የሆኑ የእርሱ ቤተሰብ መሪዎችን፣ ፈልጎ ወደፊት በመጨረሻ የሚድኑትን በጎች ለዘለአለም ከእግዚአብሔር አብ፥ የመጀመርያ ልጁ ከሆነው ክርስቶስ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመንግሥተ ሰማያት የሚሳተፉትን እንዲፈልጉ ልኳል።

ክርስቶስ የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆንን ሁላችንን፥ ሌሎችን እኛ የምናደርገውን የሚያደርጉ የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ እንድንፈልጋቸው ያዛል።[2] ይህን በማቴዎስ ወንጌል 28፥18-28 በሚከተሉት ቃላት እንዲህ ይላል፦ “ስልጣን ሁሉ በሰማይ እና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱ እና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው [ዉሃ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በማጥለቅ[3]] ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዙሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋራ ነኝ።” ይህ ክርስቶስ ሰውን ሲፈልግ ነው እንጂ ሰው እግዚአብሔርን ሲፈልግ አይደለም። ሰው እግዚአብሔርን ሲፈልግ “ሃይማኖት” ነው፥ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈልግ “ደህንነት” ነው።

ሁሉም ሃይማኖቶች ያልዳኑ ሰዎች አምላክን ወይም አምላክ ነው ብለው ያሰቡትን እንዲፈልጉ ያዛሉ። ሃይማኖት ምንድነው? ሃይማኖት ሰው አምላክ ነው ብሎ በሚያስበው ማመን እና እርሱን መፍራት ነው። በሰው ህሊና ውስጥ የሆነ አይነት አምላክ እንዳለ ይታሰባል፥ ነገር ግን ብቸኛው እውነተኛውን አምላክ አያውቀውም። ለዚህ ነው በማቴዎስ ወንጌል 28፥19 ውስጥ ኢየሱስ በዚያን ጊዜ የነበሩትን እና በአሁኑ ጊዜ ያለነውን ደቀ መዛሙርቱን “እንግዲህ ሂዱ እና አህዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ [የሚያመልኩት ትክክለኛ አምላክ ማን እንደሆነ እና እሱን ብቻ እንዲያመልኩ እና እንዲያገለግሉ] በአብ፥ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ [በውሃ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በማጥለቅ]” ያለው።

መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ፍጹም መሆን አለብን።[4] ፍጹም መሆን እንችላለን፥ ምክንያቱም ፍጹም እንድንሆን እግዚአብሔር ስለሚያዘን፥ እግዚአብሔር ደግሞ ልንሆን የማንችለውን ነገር እንድንሆን አያዘንም።[5] ኢየሱስ በማቴዎስ 5፥48 እንዲህ ይላል “እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም

*(በገጽ 2 ይቀጥላል)*

**1** ኢሳ. 1:11-16፥ 29:13-14፥ ኤር. 7:8-11፥ 23:33-40፥ ሕዝ. 13:1-23፥ ሚክ. 3:11፥ ማቴ. 6:5፥ 7-8፥ 7:21-23፥ 15:7-9፥ 21:28-32፥ 23:1-37፥ ሉቃ. 6:46፥ 18:10-14፥ ዮሐ. 5:40፥ 6:35-58፥ 10:1-15፥ 14:6፥ 15:2፥ 2 ጢሞ. 3:1-7፥ ቲቶ 1:16፥ ያዕ. 2:19 **2** ዳን. 12:3፥ ማቴ. 10:7-8፥ 28:19-20፥ ሉቃ. 24:46-48፥ ሐዋ. 1:8፥ 2:38-41፥ 10:39-43፥ ሮሜ. 7:4፥ 10:13-15፥ 1 ቆሮ. 1:17-18፥ 21፥ 9:16-17፥ ኤፌ. 3:2-10፥ ቆላ. 1:25-29፥ 2 ጢሞ. 4:2፥ 5 **3** ማቴ. 28:19፥ ሮሜ. 6:3-5፥ ቆላ. 2:10-12 **4** ዘዳ. 18:13፥ 1 ነገ. 8:61፥ መዝ. 119:1-3፥ ማቴ. 5:48፥ 2 ቆሮ. 13:11፥ ኤፌ. 4:11-13፥ 5:25-27፥ ፊል. 3:12-15፥ ቆላ. 1:21-22፥ 1 ጢሞ. 6:14፥ 2 ጢሞ. 3:16-17፥ ያዕ. 1:4፥ 1 ዮሐ. 3:6-10፥ ራእ. 21:7፥ 27 **5** ዘፍ. 17:1፥ ዘሌ. 11:44-45፥ 19:2፥ 20:26፥ ዘዳ. 18:13፥ 1 ነገ. 8:61፥ መዝ. 15:1-5፥ 24:3-5፥ 119:1-3፥ ዮሐ. 17:17-23፥ ሮሜ 6:4-14፥ 8:1-14፥ 37፥ 2 ቆሮ. 6:14-17፥ 13:11፥ ገላ. 5:16፥ ኤፌ. 4:11-13፥ 5:25-27፥ 6:10-18፥ ፊል. 1:9-11፥ 2:12-15፥ 3:12-14፥ 4:13፥ ቆላ. 1:10-11፥ 21-22፥ 1 ተሰ. 4:6-7፥ 1 ጢሞ. 6:11-14፥ 2 ጢሞ. 3:16-17፥ ዕብ. 2:18፥ 12:14፥ 13:20-21፥ ያዕ. 1:4፥ 27፥ 1 ጴጥ. 1:15-16፥ 5:8-10፥ 1 ዮሐ. 2:14፥ 3:5-10፥ 4:4፥ ራእ. 3:1-5፥ 7:13-15

## በደህንነት እና በሃይማኖት መካከል ያለ ልዩነት

(ከገጽ 1 የቀጠለ)

እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።" በመንፈስ ቅዱስ ከተመራን ፍጹም ነን። ሮሜ 8፥1-2 እንዲህ ይላል "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም [ሲኦል የለባቸውም፥ የእሳት ባሕር የለባቸውም]። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የህይወት መንፈስ ህግ ከኃጢአት እና ከሞት ህግ አርነት አውጥቶኛልና።" መጽሐፍ ቅዱስ ከግብረ-ገብ ህግ ነጻ ልንሆን እንችላለን አይልም። ከኃጢአት እና ከሞት ህግ ብቻ ነጻ መሆን እንችላለን። የኃጢአት እና የሞት ህግ እንደሚለው ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ እንደገና ከተወለድን በኋላ የግብረ-ገብ ህግን ብንተላለፍ ለኀጢያት የሚሆን መሥዋእት (ይቅርታ) የለም።

ዕብራውያን 10፥26-31 እንዲህ ይላል "የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጥያት መሥዋእት አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም [የእግዚአብሔር ጠላቶች] ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ። የሙሴን ህግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራትን እመልሳለው ያለውን እናውቃለንና፤ ደግሞም፦ ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል። በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።" ለዚህ ነው እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ የሆነው።[6] እርሱ የሚለንን ማድረግ አለብን፥ ከሃይማኖቶች መራቅ እና እንደገና በመንፈስ መወለድ። ይህ እርሱ ከእኛ የሚፈልገው መረዳት ነው፤ እግዚአብሔርን መፍራት መረዳት ነው።

በዩሐንስ ወንጌል 3፥5 ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ከመንፈስ መወለድ እንዳለበት ነግሮታል። ኢየሱስ የሆነ አይነት ሃይማኖት ውስጥ መግባት እንዳለብህ መቼም አልተናገረም በክርስቶስ ማመን እንደሌላ አይነት ሃይማኖት አይደለም። እንደገና፥ በክርስቶስ ማመን አምላክ ሰውን ሊፈልግ ሲመጣ ማለት ነው፥ ሰው እሱን እንዲያገለግል በመፈለግ።

ሰዎች በተደጋጋሚ "በክርስትና እና በሃይማኖት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?" በማለት ይጠይቃሉ። "ክርስትና ሃይማኖት ነው?" በማለት ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህን ጥያቄ በሐቀኝነት ለመመለስ፥ ክርስትና ሃይማኖት አይደለም እላለሁ። እውነተኛ ክርስትና ደህንነት ነው። ምንም እንኳን በመንፈስ ላልበራላቸው ክርስትና በአለም ካሉ ከአምስቱ ሃይማኖቶች እንደ አንዱ ቢቆጠርም፥ እውነታው በክርስቶስ ማመን በሃይማኖት ማመን አይደለም። ይህን እንዲህ በማለት ማብራራት እንችላለን፥ በእውነት በክርስቶስ የሚያምኑ ናቸው እንጂ ክርስትያኖች፥ ክርስትና ተብሎ የሚታመነውን ሃይማኖት የሚከተሉት አይደሉም። እስከ አሁን ድረስ ሃይማኖቶች በሃይል ክርስትናን የመቃወም ታሪክ አላቸው።

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሶስት የተለያዩ የምርመራ ወቅቶች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን ገድላለች። እንዲሁም ባለፉት ሁለት ሺህ አመታት ተጨማሪ የተለያዩ ግድያዎችን ፈጽማለች፥ ለምሳሌ ብዙ ህጻናት ከእናቶቻቸው እና ከአባቶቻቸው ጋር የተገደሉበት የዋኮ (በቴክሳስ ውስጥ የሚገኝ ከተማ) የጅምላ ጭፍጨፋ አይነት። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእንደዚህ አይነት ተግባራት ቀጥላለች።

መለስ ብለን የስፔን ምርመራን ጨምሮ የተለያዩ በቫቲካን የተፈጸሙ የጭካኔ ተግባራትን መመልከት እንችላለን። ይህ በአውሽቪትዝ (በፖላንድ ውስጥ የሚገኝ ከተማ) እና በተለያዩ የናዚ የማጎርያ እስር ቤቶች የተገደሉ ስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያንን ያጠቃልላል። በአሁኑ ሰዓት በክርስትያኖች ላይ ያለው ጦርነት የሚመጣው ከቫቲካን ነው።[7] ብዙዎቻችን በመቶዎች ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠሩ መሬት እና ሕንጻ ተወስደውብናል፥ እንዲሁም እውነተኛ ዳግም የተወለደን ክርስትያኖች በካቶሊክ ሃይማኖት ምክንያት በሃሰት ክስ የእድሜ ልክ እስር በወህኒ ቤት እየፈጸምን ነው። የሮማ ካቶሊክ አምልኮ ስለሚሄዱ ትናንሽ አዛውንት እናቶች እና አባቶች እያወራሁ አይደለም። እነርሱ እንደሌላው የአሁኑ አለም ሰዎች ሁሉ ስለዚህ እውነታ የሚያውቁት ነገር የለም። ቢሆንም የምለው ነገር እውነት ነው።

በፖላንድ ውስጥ የካቶሊክ እና የሉተራኖች ደውሎች በሚያቃጭሉበት ወቅት በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ በጀርመን የጋዝ ማጠራቀምያ እና እቶን ውስጥ እየሞቱ፥ ከዛም ወደ ሰፋፊ ጉድጓዶች (ጅምላ መቃብሮች) ይገፉ ነበረ። አንድ አንዶች ሲቀበሩ በህይወት እንደነበሩ ተነግሮኛል። ተመልካቾች ሁሉንም አይተዋል፥ እንዲሁም ተመልካቾች ሁሉንም ሰምተዋል።[8] እግዚአብሔር ሁሉንም አይቷል፥ እንዲሁም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰምቷል።[9] በቅርቡ ስለሚመጣው የፍርድ ቀን እግዚአብሔር ይመስገን።[10]

6 ኢዮ. 28:28፥ መዝ. 111:10፥ ምሳ. 1:7፥ 9:10፥ 15:33

7 ዳን. 7:7፥ 19-27፥ ራእ. 13:1-7፥ 17:1-18 8 ኤር. 4:16፥ ዳን. ምዕራፍ 4፥ ማቴ. 13:24-30፥ 36-43፥ 47-50፥ 24:29-31፥ ሉቃ. 15:4-10፥ 1 ቆሮ. 11:10፥ 1 ጢሞ. 5:21፥ ራእ. 14:13-20 9 ዘዳ. 31:21፥ 2 ነገ. 19:27፥ 1 ዜና 28:9፥ ኢዮ. 31:4፥ 34:21-22፥ 25፥ መዝ. 44:21፥ 139:1-6፥ 12-16፥ ምሳ. 15:3፥ 11፥ ኢሳ. 29:15-16፥ ሉቃ. 16:15፥ ዕብ. 4:13፥ 1 ዩሐ. 3:20 10 መክ. 12:13-14፥ ዳን. 7:9-10፥ ማቴ. 3:12፥ 24:3-15፥ 29-44፥ ማር. 4:22፥ ሮሜ 2:5-13፥ 16፥ 14:10-12፥ 2 ቆሮ. 5:10-11፥ 2 ተሰ. 1:7-10፥ 2 ጢሞ. 4:1፥ 8፥ ዕብ. 10:30-31፥ ይሁ. 14-15፥ ራእ. 1:7፥ 11:18፥ 20:11-15

## ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ

*(ከፈረንሳይኛ የተተረጎመ)*

በአገልግሎትህ እንደተቀበልን እንቆጠራለን!

ጀግንነት አቋም መያዝ ነው:። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ይህን ሃሰተኛውን ክርስቶስ፥ ተቆጣጣሪ መንግስትን ከምታቀርብበት መንገድ በመነሳት የክርስቶስ ወታደር እንደሆንክ እየተረዳሁ ነው:። ደፋር እንደሆንክ ይህ ያሳያል። ትንሽ ድፍረት፤ አሸናፊ ነህ፣ ይህን ደግሞ ታውቃለህ።

የስነ-ጽሁፍ እርዳታን እንቀበላለን። መልካም ፋሲካ ለሁሉም ክርስትያኖች ከአላሞ አገልግሎቶች።

ዚጋሻኔ ማሮዬ እስራኤል
ሱድ ኪቩ አውራጃ ፣ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ

ሉቃስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 1 እስከ 5 እንዲህ ይላል “በዚያን ጊዜ የህዝቡ አእላፍ እርስ በርሳቸው እስኪረጋገጡ ድረስ ተሰብስበው ሳሉ፥ ለደቀ መዛሙርቱ [ኢየሱስ] እንዲህ ይል ጀመር፦ አስቀድማችሁ ከፈርሳውያን [ሃይማኖተኛዎቹ አይሁዶች] እርሾ ተጠበቁ፥ እርሱም ግብዝነት [ኃጢአት] ነው። ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም። ስለዚህ በጨለማ የምትናገሩት ሁሉ በብርሃን ይሰማል [በተመልካቾች እና በእግዚአብሔር]፥ በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ የምትናገሩት በሰገነት ላይ ይሰበካል። ለእናንተም ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፥ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ።እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ፥ እርሱን ፍሩ [ታላቁ እግዚአብሔር]።”

እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለበት ወደማያውቀው አዳም መጣ። ለዘላለም እንዲኖር ከህይወት ዛፍ እንዲበላ እግዚአብሔር ነገረው፥ እርሱ ግን እግዚአብሔር አትብላ ካለው መልካምን እና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ በላ።[11] እንደገና እግዚአብሔር ከደህንነት እውቀት ጋር ወደ አዳም መጣ፤ አዳም ግን የሰይጣንን ሃይማኖት (እውቀት) መረጠ። እግዚአብሔር አንተን ጨምሮ ወደ አለም ሁሉ ከደህንነት እውቀት ጋር ይመጣል፤ ነገር ግን ቅማሎች በእንስሳት እና በሰዎች ቆዳ ላይ አንተም የተወሰነ የሰይጣን ሃይማኖት ላይ ልትጣበቅ ትችላለህ፥ አትጣበቅም?

እግዚአብሔር ወደ ሴት (ሶስተኛው የአዳም ልጅ) በደህንነት እውቀት መጣ፥ ሴትም እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመረ። ከዛም ከእግዚአብሔር ጋር ወደተመላለሰው ወደ ሄኖክ መጣ እናም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዲሆን ወደ መንግሥተ ሰማያት ወሰደው።[12] ከዛም እግዚአብሔር ወደ ኖህ መጣ።[13] ኖህም ሆነ ሌሎቹ ወደ እግዚአብሔር አልመጡም። እግዚአብሔር ወደ እነርሱ መጣ እንጂ። አብርሃም ጣዖት አምላኪ ነበረ፥ የሃይማኖት አባል፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ እርሱ መጣ።[14] ሙሴ ወደእግዚአብሔር አልመጣም፤ እግዚአብሔር ተገለጠ እና ወደ ሙሴ መጣ።[15] እግዚአብሔር ወደ ሌሎች መቶዎች መጣ፥ እንደ ደቀመዛሙርቱ አይነቶች። ወደ ሃይማኖተኛው ሐዋርያ ጳውሎስ እንዲድን በማድረግ መጣ።[16] ጳውሎስ በደህንነቱ ለእግዚአብሔር ጠቃሚ ሆነ፥ ከጨለማ ሃይላት ጋር መልካሙን ውጊያ መዋጋቱን፥ የአዲስ ኪዳንን ሁለት ሶስተኛ ያህል መጻፉን ያጠቃልላል። እነዚህ ሁሉ በእውነተኛ ደህንነት ውስጥ ተካተዋል።

በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ሶስት ዕብራውያን ልጆች (ሲድራቅ፥ ሚሳቅ እና አብድናጎ) ወደ እቶን እሳት ውስጥ ተጥለው ነበር ምክንያቱም የንጉሱን የወርቅ ጣዖት ስላላመለኩ፥ የንጉሱ ሃይማኖት አባል መሆንን በመቃወማቸው ምክንያት።[17] “መሳፍንቱ እና ሹማምንቶችም አዛዦቹ እና የንጉሱ አማካሪዎች ተሰብስበው እሳቱ በነዚያ ሰዎች [አካል ላይ] ሃይል እንዳልነበረው፥ የራሳቸውም ጠጉር እንዳልተቃጠለች፥ ሰናፌላቸውም እንዳልተለወጠ፥ የእሳቱም ሽታ እንዳልደረሰባቸው አዩ። ናቡከደናጾር መልሶ፦ መልአኩን የላከ፥ ከአምላካቸው በስተቀር [ምንም ሃይማኖት] ማንንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉሱንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባርያዎችን ያዳነ፥ የሲድራቅ እና የሚሳቅ አብድናጎም አምላክ ይባረክ” (ትንቢተ ዳንኤል 3፥27-28)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሐዋር

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*

11 ዘፍ. 2:16-17፥ 3:1-6

12 ዘፍ. 5:22-24፥ ዕብ. 11:5 13 ዘፍ. 6:11-18፥ 22፥ ዕብ. 11:7 14 ዘፍ. 12:1-8፥ 17:1-9፥ ሐዋ. 7:2-3፥ ዕብ. 11:8 15 ዘጸ. ምዕራፍ 3፥ ሐዋ. 7:29-34 16 ሐዋ. 9:1-22፥ ገላ. 1:13-19 17 ዳን. ምዕራፍ 3

## ማላዊ

ውድ የቶኒ አላሞ አገልግሎቶች፥

በመጀመሪያ እና በቅድሚያ ሰላምታዬ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ይድረሳችሁ። ደህና እንደሆናችሁ ተስፋ አደርጋለሁ እና አምናለሁ። በእኛ በኩል የምናማርረው ነገር የለም።። ጌታ በቀን እና በሌሊት እየመራን ነው።

ሁልጊዜ የቶኒ አላሞን ፅሁፍ ስናከፋፍል እና ስንመሰክር ልክ በሐዋርያት ሥራ 1፥8 እና በማርቆስ 16፥15-16 ውስጥ እንደነበረው በመንፈስ ቅዱስ እንነካለን፥ ምክንያቱም ፓስተር ቶኒ በስነ-ጽሁፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በመጽሐፍት ስብከት አለምን እንዲደርስ በሀያሉ አምላክ ስልጣን ስለተሰጠው ነው። እኛም ይህን ስልጣን በአደባባይ ሁሉ ስናደርስ፣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር በእርግጥ እየተመለሱ ነው፤ ሙስሊሞች፥ የሂንዱ እምነት ተከታዮች፣ የጀሆቫ ምስክሮች፣ ወ.ዘ.ተ.፤ በከተማዎች፣ በገጠሮች እና በእስር ቤቶች ውስጥ ያሉ።

እዚህ ማላዊ ያለን ፓስተር አላሞን በየቀኑ በጸሎታችን እናስበዋለን፤ ምንም እንኳን በእስር ቤት ውስጥ ያለ ቢሆንም አንድ ቀን በጌታ ስም ይፈታል። ጠበቃዎች የችሎቱን ቀን በመቀየር ላይ ናቸው፥ ማየት ተስኖታል፥ ነገር ግን በእነዚህ ነገሮች ሁሉ መጨነቅ የለበትም፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር ይችላል እናም አንድ ቀን ከእነዚህ ፈታኝ ጊዜያት ይወጣል። ኢዮብ እና ዮሴፍ በአንድ አንድ ፈታኝ ጊዜያት አልፈዋል። ዮሴፍ በዘመዶቹ ተሸጦ ነበረ፥ እግዚአብሔር ግን አስነሳው። ስለዚህ የአሜሪካ መንግስት ፓስተር አላሞ በፈታኝ ጊዜ እንዲያልፍ እያደረገው ከሆነ እግዚአብሔር በቁጥጥር ላይ ነው። አንድ ቀን ሁሉ ነገር በጌታ ስም ደህና ይሆናል።

በቀን እና በሌሊት ለእናንተ እየጸለይን ነው፥ እንዲሁም ቶኒ ከእስር እስኪፈታ ድረስ እየጾምን ነው።

በጌታ የእናንተ፥
ፓስተር ዳንሌክ ሃሪ ሚተፓ
የቶኒ አላሞ አገልግሎቶች፥ ብላንታየር ከተማ፥ ማላዊ፥ አፍሪካ



የአላሞ አገልግሎቶች በኢንተርኔት
www.alamoministries.com

## በደህንነት እና በሃይማኖት መካከል ያለ ልዩነት

(ከገጽ 3 የቀጠለ)

ያው ዩሐንስ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ አልፏል። በፈላ ዘይት ውስጥ ተጨመረ፥ ነገር ግን አልተቃጠለም። ከመፍላቱም የተነሳ አልሞተም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ ሁሌም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ምክንያት እግዚአብሔር ቀድሞ ስለተገናኘው መሆኑ ድንቅ ነው። እግዚአብሔር ኢዮብን ሊያገኘው ቀድሞ መጣ፥ ኢዮብም እርሱን አገለገለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው ቀድሞ እግዚአብሔርን ሰለማገልገል ስላሰበ እግዚአብሔርን ያገለገለበት የትኛውም ሁኔታ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን ለመፈለግ ስለመምጣቱ ብቻ ይናገራል አንድ ቀን ኢሳይያስ ራእይ አየ፤ እንዲሁም የጌታ ድምጽ እንዲህ ሲል ሰማ "የጌታም ድምጽ፡- ማንን እልካለው? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማው። እኔም፡- እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ አልሁ" (ትንቢተ ኢሳይያስ 6፥8)። ኤርምያስ ራእይ ካየ በኋላ፥ ጀሆቫ ያዘዘውን ቃላት በትንቢት ለእስራኤላውያን ሊናገር ተነሳ (ትንቢተ ኤርምያስ 1፥4-19)። ዳንኤልም ጀሆቫ ኢየሩሳሌምን እንዲመልስ ለመጾም እና ለመጸለይ ከመነሳቱ በፊት ራእይ አየ (ትንቢተ ዳንኤል ከምዕራፍ 7-9)። ሰው እግዚአብሔርን ከማገልገሉ በፊት እግዚአብሔር ቀድሞ ወደ ሰው እንደሚመጣ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያሳያል።

ምንም አይነት ማስተባበያ እንዳይኖራችሁ በእኔ እና በሌሎች በዳኑ ፓስተሮች እና ወንጌላውያን በኩል እግዚአብሔር እያገኛችሁ ነው። በዳንን በእኛ ውስጥ የሚኖረው እና የሚሰራው የእግዚአብሔር መንፈስ ለሃይማኖት ሳይሆን ለራስህ እና ለሌሎች መዳን እንዲሆን አንተን ሊያገኝህ እየተከታተለህ ነው።

ሮሜ 10፥12-15 ከእግዚአብሔር ወደ አለም የተላኩ ሰባኪዎች መላክ ያለባቸው፥ ሰዎች ለመዳን በእነዚህ ቃላት እንዲያምኑ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፡- "በአይሁዳዊና በግሪክ [አህዛብ] ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉም ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ባለጠጋ ነው፤ የጌታንም ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምስራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?"

እንደገና ኢየሱስ እኛን ወደ አንተ ልኳል። እግዚአብሔር እየፈለገህ ነው፤ አንተ አይደለህም እግዚአብሔርን የምትፈልገው። ይህ እውነታ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1-12 እንዲህ ተገልጿል "ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፥ [ደቀ መዛሙርቱን] ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው። አላቸውም። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት። ሂዱ፤ እነሆ፥ እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ፤ በመንገድም ለማንም እጅ አትንሡ። ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ። በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር፥ ሰላማችሁ ያድርበታል፤ አለዚያም ይመለስላችኋል። በዚያም ቤት ከእነርሱ ዘንድ ካለው እየበላችሁና እየጠጣችሁ ተቀመጡ፤ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና። ከቤት ወደ ቤት አትተላለፉ። ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ፥ ያቀረቡላችሁን ብሉ፤ በእርስዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና። የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው። ነገር ግን ወደ ምትገቡባት ከተማ ሁሉ ባይቀበሉአችሁ፥ ወደ አደባባይዋ ወጥታችሁ። ከከተማችሁ የተጣበቀብንን ትቢያ እንኳን እናራግፍላችኋለን፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ወደ እናንተ እንደ ቀረበች ይህን እወቁ በሉ። እላችኋለሁ፥ በዚያን ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ይቀልላታል።"

በሃይማኖት የሚያምኑት አምላክ ነው ብለው የሚያስቡትን ሊያገለግሉ ቀድመው እርምጃ ይወስዳሉ፥ በክርስቶስ የሚያምኑት

## ሃይቲ

(ከፈረንሳይኛ የተተረጎመ)

ውድ ቶኒ አላሞ፥ የእግዚአብሔር አገልጋይ፥

ጌታ ኢየሱስ በሁሉም አገልግሎት መስከ ጨምሮ ይርዳህ፥ በተለይ በወንጌል ሥርጭት፥ በአለም ሁሉ ውስጥ ያሉ ነፍሳትን ለኢየሱስ ለማግኘት። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እንዲያድግ እንድናደርግ ይረዱን ዘንድ ስለላክልን እቃዎች (ጽሁፎች፥ የመሲህ መጽሃፍት እና መጽሐፍ ቅድሶች)በጣም አመስጋኞች ነን። እናመሰግናለን። መንግሥተ ሰማያት ባዶ አይደለችም፤ ጌታ ይህን ልብ ብሏል። የኢየሱስ ክርስቶስ እጮኛ ቡድን ተብሎ የሚጠራው የእኛ ቤተ ክርስቲያን በጌታ ኢየሱስ ስራ አንተን ለማበረታታት በፓስታ ውስጥ በቅርቡ አንድ አስገራሚ ነገር ይልክልሃል። ይህን አስገራሚ ነገር ስትቀበል ንገረን።

በሚከተሉት ቀናት ጽሁፎችን በወንጌል ስርጭት መልክ ለማከፋፈል እንፈልጋለን፡- በሚያዝያ 1፥2፥7፥8 እና 10፥ 2013፤ ታላቁ የወንጌል ስርጭት ዘመቻ በፖንት - ሮዥ ብለን ጠርተነዋል። ሁለት ቀን በድምፅ መሣሪያ የታገዘ ከቤት ውጪ የሚደረግ አገልግሎት እና የሶስት ቀናት የወንጌል ስርጭት ለጌታ ይኖረናል። ሰይጣን በእኛ ላይ ጦርነት ሰለ አስነሳ፥እባክህ በጸሎት እርዳን፥ ድሉ ግን የእኛ ነው።

ጽሁፎችን ስንጨርስ እንደገና እንዲላክልን እናሳውቅሀለን።

ለአንተ መጸለያችንን እንደቀጠልን ነው እናም አትጨነቅ፥ በክርስቶስ ውስጥ ተሰውረሀልና። ድሉ የአንተ እና የቤተሰቦችህ ነው።

ሁልጊዜ በመቀደስ፥ በምልጃ፥ በጾም እና በወንድማዊ ፍቅር ቆይ። ከዚህ ጠማማ ትውልድ እራስህን ጠብቅ።

ሴዛር ፍራንሲስ ጁንየር<br>
ዋና አስተባባሪ (የክርስቶስ እጮኛ ቡድን)<br>
*ፖንት - ሮዥ፥ ሃይቲ*

ዳግም በእግዚአብሐር ከፍ ካሉ እና ከተነኩ በኋላ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ። በዚህ ምክንያት ልብወለዳዊ የሆነን አምላክ ለማገልገል ሰው መፍጠን የለበትም እላለሁ፤ ባዶ ሃይማኖትን ለማገልገል። እግዚአብሐር እርሱ በመንፈሱ በውስጣችን ሲሆን ብቻ እግዚአብሐርን እናገለግላለን።[18] እግዚአብሐር አስቀድሞ በውስጣችን ሳይኖር ብናገለግለው በሃይማኖት ውስጥ እንጂ በደህንነት ውስጥ አይደለንም። በምሳሌ ለመናገር፥ ብዙ ሰዎች ዛሬ በውጪ “ክርስትያን” የሚል ምልክት ሰቅለው በውስጥ ግን በሃይማኖት ድርጅት ውስጥ ይሳተፋሉ። በራሳቸው አእምሮ ክርስቲያን ናቸው፥ በእውነታው ግን ሃይማኖታዊ ብቻ ናቸው።

ክርስቲያን ምንድን ነው? ክርስቲያን በውስጡ ክርስቶስ በመንፈስ የሚኖርበት እና የሚሰራበት እንዲሁም እግዚአብሐርን እንዲያገለግል በመንፈስ ቅዱስ የሚንቀሳቀስ ነው።[19] በሌላ ወገን ደግሞ፥ የሃይማኖት ሰው አምላክን እያገለገልኩ ነው ብሎ የሚያምን እና አምላክ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ለማድረግ የሚፈልግ ነው። ይህ ብዙ ክርስቲያን ነን ብለው የሚያምኑ የሚያደርጉት ነው። ክርስቲያን ነን ብለው ይናገራሉ፥ ነገር ግን ዳግም አልተወለዱም። ስላልዳኑ ክርስቶስን አያውቁትም፥ እናም እግዚአብሐርን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው አያውቁም። ሊሰሙት ስለማይችሉ ክርስቶስን መከተል አይችሉም።[20] ስለዚህ በራሳቸው ፍቃድ የሚመሩ ናቸው፥ እናም እውነተኛ አምላክ ሊጠቀምባቸው አይችልም። እርባና የለሽ ናቸው። ነገር ግን በእውነተኛ ክርስትያኖች ልምምድ ውስጥ በሁሉ ነገር የሚመራቸው ጌታ ነው። በቀላሉ “አዎ። አሜን።” ይላሉ። ጌታ መሪያቸው እና አምላካቸው ነው። ይህ ከሃይማኖት ሰዎች መንገድ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው።

ጌታ በደማስቆ መንገድ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስን ካገኘው በኋላ የተናገራቸው የመጀመሪያ ቃላት “ጌታ ሆይ፣ማን ነህ?” ነበር:: (ጳውሎስ ጌታ እንደሆነ አውቆ ነበር አልያማ፥ “ጌታ ሆይ፣ማን ነህ?” ብሎ ባልጠየቀ ነበር::) ጌታም “አንተ የምታሳድደኝ እኔ ክርስቶስ ነኝ [ማንም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላትን ሲያሳድድ የሚያሳድዱት ክርስቶስን ነው:: የዚህ ምክንያት የእርሱ አካል፥ የእርሱ ቤተ መቅደስ፥ የክርስቶስ አካል ስለሆንን ነው]” አለው:: አንደኛ ቆሮንቶስ 3፥16-17 እንደሚነግረን “የእግዚአብሐር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሐርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሐርን ቤተ መቅደስ [የጌታ አካል፥ እኛ] ቢያፈርስ እግዚአብሐር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሐር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።” አንተ የሞተ ሃይማኖት እየተከተልክ አይደለህም:: ክርስቶስ ከአብ ጋር በመንፈስ የማይኖርበት ሃይማኖት ስለማትከተል ከተል ቅዱስ ነው፥ የዳንክ፥ ዳግም የተወለድክ ክርስቲያን ስለሆንክ የእግዚአብሐር ቤተመቅደስ ነህ። ለዚህ ነው እግዚአብሐር የሚኖርበት አካል ቅዱስ የሆነው እና እግዚአብሐር የማይኖርበት አካል ቅዱስ ያልሆነው። በእግዚአብሐር ፍርድ ቤት ውስጥ ስትሆን ከምንም ነገር ይልቅ ቅዱስ መሆን ትፈልጋለህ::

አለም ሃሳብን በሚያዘቡ እና በሚያስቀይሩ ነገሮች የተሞላች ናት። በአለም ላይ አስፈላጊ ከሆነው ብቸኛ ነገር፥ እርሱም ነፍስን በእግዚአብሐር አገልግሎት ውስጥ ማቆየት እና ክርስቶስን ከአብ ጋር በውስጥህ እንዲኖር ማድረግ ከሆነው፥ አእምሮህን ከዚያ ነገር ዞር ማድረግ የሰይጣን ማዛብያ ዘዴ ነው። “እስትንፋሱ በአፍንጫው ያለበትን ሰው ተውት፤ እርሱ ስለምን ይቆጠራል?” (ትንቢተ ኢሳይያስ 2፥22)።

የአንተ ምርጫ ይህ ነው፡- የእግዚአብሐር ቅዱስ አካል መሆን ትፈልጋለህ ወይስ እንደሌላው ያልተቀደሰ፥ ሰይጣን የሚኖርበት አካል

*(በገጽ 8 ይቀጥላል)*

**18** ሕዝ. 36:27፥ ዮሐ. 14:15-20፥ 23፥ 26፥ 15:1-11፥ 26፥ 16:7-14፥ ሮሜ 8:1፥ 10-11፥ 26-28፥ 1 ቆሮ. 3:9፥ 16-17፥ 6:19-20፥ 2 ቆሮ. 6:16-18፥ ኤፌ. 2:18-22፥ ፊሊ. 2:12-13፥ ቆላ. 1:27-29፥ 2 ጢሞ. 1:14፥ 1 ዮሐ. 4:4፥ 5:12 **19** ኢሳ. 30:21፥ ዮሐ. 15:1-5፥ 17:21-23፥ 26፥ 1 ቆሮ. 15:10፥ 2 ቆሮ. 5:17-21፥ ገላ. 2:20፥ ኤፌ. 3:16-21፥ 1 ዮሐ. 2:20፥ 27 **20** ዮሐ. 8:42-43፥ 10:27

## አርከንሳስ

*ፓስተር ቶኒ፥*

ከጥቂት ቀናት በፊት፥በኒውኦርሊንስ የሆቴል ስራ አስከያጅ የሆነችው ቬራ ደውላልኝ ነበር ወንድሞች እና እህቶች እርዳታ ባስፈለጋቸው ጊዜ የምትረዳቸው እሷ ነበረች፥ ለምሳሌ በኒወርሊንስ ቀዶ ጥገና እና ወደ ሆስፒታል መሄድ ሲያስፈልጋቸው።

ከሆቴል ሰራተኞች ጋር ችግር በነበረባት ጊዜ የሰጠሃትን ምክር እረስታ አታውቅም። እንዲህ ብለህ ነግረሀት ነበር፥ “ስራ የሚያስፈልጋቸውን ክርስትያኖች ለምን አትቀጥሪም እና አብራችው ጌታን አትፈልጉም? ንግድሽ እንደሚበለጽግ አምናለሁ።” ቬራ ምክርህን ወድያው ተቀበለች እና በአጭር ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ ክርስትያኖች ሙሉ ሰራተኞች ኖርዋት፤ በየቀኑ ከስራ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ እና አብሮ ለመጸለይ የሚገናኙ።

ተአምር ሆነ፤ ሁሉም ሰው በታታሪነት አብረው ሰሩ፥ በደስታ አጸዱ፥ እቃዎችን ጠገኑ እናም ሆቴሉ ማበብ ጀመረ እና ሽልማት ከክልሉ ቢሮ አገኙ።

ካትሪና የተባለው አውሎ ንፍስ ኒው ኦርላንስን በመታበት ምሽት ጌታ ቬራን በ 1:00 ኤ.ኤም. ላይ ከእንቅልፍ አነቃት። የባልዋን እና የእሷን ልብሶች እንዲሁም አንድ አንድ መገልገያዎችን ወደ መኪና ውስጥ በማስገባት ወደ ጃክሰን፥ ሚሲሲፒ እንድትሄድ ነገራት፥ “አሁኑኑ፥ በፍጥነት!!!” በገልፍ ኮርት ያለው ቤታቸው በዚያን ወቅት ተሸጦ ስለነበረ እሷ እና ባልዋ ያንን ምሽት በሆቴል ውስጥ እያሳለፉ ነበረ።

ጌታ ያን ጊዜ ብቻ አይደለም ህይወቷን ያተረፈው፥ ነገር ግን ከጡት ካንሰር የዳነች ናት። ፓስተር ቶኒ፥ አንተ እንዳልከው፥ ለብዙ አመታት የነበሩትን ወንድሞች እና እህቶች ማቆያ ክፍል ሆቴል በመስጠት ምህረት አሳየች እናም እግዚአብሔር በእርስዋ ላይ ምህረት አደረገ።

እግዚአብሔር የሰጠህን መልእክቶች በሲዲ ትሰማለች እናም በጌታ እንደምትወድህ እንደም ታውቅ ማረጋገጥ ፈለገች፥ እየጸለየችልህም ነው፥ እግዚአብሔር አንተ የጌታ ስለሆንክ እና ብዙ ምህረት ስለዘራህ ታላቅ እንቅስቃሴ እንደሚያደርግልህ ታምናለች።

ጌታ ይመስገን።

ሜሪ አኒ — ቴክሳርካና፥ አርከንሳስ

## ህንድ

በክርስቶስ ውድ ወንድሞቻችን፥

ስብሰባዎቻችን በአስደናቂ ተአምራት እንደተጠናቀቁ ለጌታ ክብር እነግራችኋለሁ ከአንድ ሺህ በላይ አባላት ተሳትፈዋል። ጽሁፎቻችሁን በስብሰባዎቹ ወቅት ለብዙ ለተሰበሰቡ ሰዎች አስተዋውቀናል እንዲሁም ብዙ አባላት ጌታን ተቀብለዋል።

ክብር ለጌታ ይሁን። ስለፓስተራችን ጉዳይ ሁሉም ጸልየዋል። ለእኛ ጸልዩልን።

ወዳጅ ወንድማችሁ፥

ሶልማን ራጁ ኮላ　　　　አንድህራ ፕራድሽ፥ ህንድ



## ፊሊፒንስ

"የጥርስ መፈጨት እና ማፋጨት" ስለተሰኘው አስደናቂ ጽሁፍ፥ ፓስተር ቶሚ፥ በጣም እናመሰግናለን። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ስነ ስርአትን ስለሚያካትት በጣም ወድጄዋለው።

በአሁኑ ጊዜ በአለም ዙርያ ላሉ ክርስትያኖች ስነ ስርአት በጣም ያስፈልጋል።

ፓስተር ሲሲልዩ ኤች. አሲስ፥ ዳግማዊ　　　　አልባይ፥ ፊሊፒንስ



*ዳራኮንዳ ቪድያ ሳጋር ወደ ቴሌጉ ቋንቋ የተተረጎሙ የፓስተር አላሞ ነፍስን ድል የሚያደርጉ ጽሁፎችን በቪሳክሀፓትናም፥ አንድህራ ፕራድሽ፥ ህንድ አካባቢ ባሉ መንደሮች እና ከተማዎች ውስጥ ያከፋፍላል*

## ካልፎርንያ

በክርስቶስ ወንድሞቼ ለሆናችሁ፥

ሁላችሁም በክርስቶስ መልካም እና ደህና እንደሆናችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ሁሌም ከኢሜል ቡድኑ ስሰማ እባረካለሁ። በጸሎታችሁ ውስጥ ሰለአለሁ አመሰግናለሁ። በጸሎቴ ውስጥ ሳትሆኑ አንድ ቀን አያልፍም፥ በተለይ ፓስተር ቶኒ። ዛሬ የጽሁፍ ሳጥን ደርሶኛል እና እስካሁን ያልነበረኝን ትልቅ ስብስብ ሰለአገኘሁ ተደሰትኩ። በእውነትም የገና ስጦታ እንደማግኘት ነበር። እግዚአብሔር በጹሁፉ ውስጥ ይሰማኝ ነበረ። "እግዚአብሔር እናት የለውም" የሚለውን አነሳሁ እና ጆሮ ያለው እንዲሰማ ጮክ ብየ ማንበብ ጀመርኩ፥ ጆሮ ያለው እንዲሰማ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

ከባለቤቴ ጋር በሎስ አንጀለስ ውስጥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ አሁን ስላለው የነዳጅ ዋጋ ሳምንት ከማይሞላ ጊዜ በፊት ስናወራ ነበር። የእናንተ ግብዣ ደርሶኛል ለመቀበል የምሞክረው ነገር ነው። የደርሶ መልስ ጉዞ ዋጋ $100 ነበር፤ አሁን ግን ደርሶ መልስ $200 ያስወጣል፥ ቢሆንም የአማልክት አምላክ እና የጌቶች ጌታ ፍቃድ ከሆነ በሆነ መንገድ በር እንደሚከፈት አምናለሁ። ሰለግብዣው አመሰግናለው። ከዚህ በፊት ቤተ ክርስቲያን በእንግድነት በምኅበኝበት ጊዜ ተባርኪያለሁ። ሻንጣየን ለሶስት ሳምንታት ጭኜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድሄድ እግዚአብሔር በድምጽ ነገረኝ። ይህ ከፍተኛ መንፈሳዊ ልምምዴ ነበረ፥ ነውም። መዝሙሩ በጣም ቆንጆ ነበር፥ በሁሉም ጉባኤም እግዚአብሔር ሲንቀሳቀስ ይሰማኝ ነበር። ሽለቆውን እያለፍኩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስነዳ የእግዚአብሔር መገኘት ይሰማኝ ነበረ፥ ያንን ልምምድ እንደገና ማግኘት እፈልጋለው። ምግቡ ምን ያህል ምርጥ እንደነበረ፥ ምስክርነቱን ሁሉ መስማት እና ከወገኖች ጋር አብሮ ወንጌልን በየመንገድ ማሰራጨት እና እንዴት እንደሚሰራ ማየቴን ሳልጠቅስ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ማንኛውን አይነት ጥያቄዎች እንዴት እንደሚመልሱ ሳይ፥ ይኔ ነው እነርሱ ያላቸው እንዲኖረኝ እንደምፈልግ ያወቅኩት። አሁን ከብዙ አመታት እና ከብዙ ጥናት በኋላ እዛ ልደርስ ነው።

እናም አዲሱ ኮከብ ጳጳሳቸው በመጀመርያ ለጉባኤው የተናገረው ነገር ወደ ድንግል ማርያም ሲጸልይ እንደነበረ ነው። እውር እውርን ወደ ጉድጓድ መራ ማለት ይህ ነው! ዋዉ! ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ። ለዛም ነው፥ "እግዚአብሔር እናት የለውም" ማንበብ ተገቢ የሆነው። ለዛም ነው ፓስተር ሁልጊዜ በህይወቴ ትክክል የሆነው። በሚቀጥለው ጽሁፌ ሰላልታወቁ በራሪ አካላት፥ ስለ ፓስተር እና ሰለ ሱዚ እና እንዴት ሁሉ ነገር በህይወቴ እንደተፈጸመ እማካፍለው የተወሰነ ምስክርነት አለኝ። በተአምራት እንደምታደርጉት፥ የበለጠ በጎችን ወደ መንጋው እንድታመጡ በአሁኑም፥ በሁሉም ቀን እንዲባርካችሁ ጌታን እጠይቃለሁ።

እግዚአብሔር ይባረክ። መልካም ምሽት።

ወንድም ቶም ሲ.　　　　ካሊፎርኒያ

## ዛምቢያ

ውድ ፓስተር፥

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለጠራህ ስራ በማድነቅ ልጀምር። ለመጀመርያ ጊዜ ከቤተ ክርስትያናቹሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሁፎችን የተቀበልኩት በ 2012 በጁን ወር አካባቢ ነበር። በአጠቃላይ 382 መጽሔቶችን እና ሌሎች ጽሁፎችን 6 የመሲሀ መጽሐፍቶችን፥ አንድ የኪንግ ጀምስ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ተቀብ ያለው። ምን አይነት ድንቅ ስራ ነው የተሰራው! ምስጋናዬን የምገልጽበት በቂ ቃላት የሉኝም፥ ነገር ግን የእናንተ ቀስቃሽ ጽሁፎች በእኔ እና ጽሁፎቹ በደረሳ ቸው ሰዎች ህይወት ውስጥ ምን ያህል እንደሰራ ሁሉን የሚያውቅ ጌታ አምላክ ምስክሬ ነው።

ጌታ እድል እና ጊዜ በሰጠኝ ቁጥር ጽሁፎች በተማሪ መኖርያዎች፥ ጉዞ በማ ደርግበት ጊዜ በአውቶብሶች ውስጥ እና፥ በአደባባይ ላይ እና በገበያ ስፍራዎች ወ.ዘ.ተ. ይበተናሉ። ይህ በወንጌል ስርጭት ወቅት ወይም በግል ጉብኝት ጊዜ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ሁሉ ለወንጌል ስርጭት ለመጠቀም አንድ አንድ ወዳጆቼ (በክርስቶስ ወንድሞቼ) የመሲህ መጽሐፍ እና ሌሎች ጽሁፎች ወሰዱ። ይህ ማለት በቀላሉ፥አንተ የጌታ ሰው፥ አነቃቂ ጽሁፎች የተለያዩ የአለም ክፍላት እንደደረሱ ሁሉ እኛም እነዚህ ጽሁፎች በእኛ ሀገር (ዛምብያ) ውስጥ እና ውጪ መከፋፈል አለባቸው ብለን እንጸልያ ለን። እናምናለንም። አዎ! ሰለ ኢየሱስ ክርስቶስ በጽሁፎችህ ውስጥ የተብራራ ውን ጸጋ የሚያነቡ እና የሚያምኑ በእርግጥም ይድናሉ!

የእግዚአብሔር ሰው፥ አንተ፥ እግዚአብሔር ሕይወቱን ለሌሎች ይሰጥ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የሚያቀጣጥልህ ፓስተር እና ወንጌላዊ ብቻ እንዳልሆንክ የእ ግዚአብሔርን ፍቅር ሚስጥሮች የሚገልጹ ጽሁፎችህ እንደሚያሳዩ መመስከር እችላለሁ። ጽሁፎችህን አንብበው ተመልሰው የመጡ ብዙዎቹ ከፓስተር አላሞ ጹሁፎች ጀርባ ሰላለው ሃይል መስክረዋል። በመንግሥተ ሰማያት ጉዳይ ለመጪ ከን ካለማወቅ የበራላቸው እና በጥበብ እየተሞሉ ነው።

ለዚህ ድንቅ ስራ የጠራህ እና ህይወታችንን እና መንገዳችንን በታላቅ እጁ የያዘው ታላቅ አምላክ (ትንቢተ ዳንኤል 5፥23) ታላቁ አምላካችን፥ አዳኙ ክር ስቶስ ኢየሱስ እስኪገለጥ ድረስ በብርታት እና ከስህተት ነጻ በማድረግ ይጠብ ቀህ። አሜን (ይሁዳ 24-25፥ ቲቶ 2፥11-15፥ 1 ቆሮንቶስ 1፥7-9)።

ሰለዚህ፥ እዚህ በተጠቀሰው መጠን የተቀቡት ጽሁፎችህን በሚቀጥሉት አመታት ወደ ቤተ ክርስቲያን መላክ ከቻለች አዲስ ልመና አቀርባለሁ። (የጹሁ ፎቹ ዝርዝሮች ተዘለዋል)።

ጥረትህ እና ከፍተኛ ፍቃደኝነትህ እጅግ ይደነቃል።

በከፍተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪ የአንተ የሆነው፥

ዚምባ ሞስስ — ሉሳካ፥ ዛምብያ

## ኒውዮርክ

ቶኒ ጥሩ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ለአርባ ሶስት አመታት አውቀዋለሁ። ጌታ ይባር ከው። ቶኒ አላሞን በግል አውቀው ነበር። ቶኒ ስለ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትክክል ነው፥ በጉዳዩ ላይ ድምጹን በማሰማቱ እና ለክርስቶስ በመሲሁ የሚያምን አይሁድ በመሆኑ ምክንያት ከፍተኛ ስደት ደርሶበታል። ቶኒ ጥሩ የክርስቶስ ሰው ነው፥ በክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ምክንያት በሰይጣን ሃይላት ከፍተኛ ችግር ደርሶበታል። ሁላችንም ልንጸ ልይለት ይገባል። ቶኒ፥ ጌታ ይባርክህ ለኢየሱስ ላለህ አቋም እና ሰይጣናዊ ክፋትን ለመ ቃወም ባለህ አቋም።

ቴድ ዋይተስ — ኒውዮርክ፥ ኒውዮርክ

## አውስትራሊያ

(ከስፔን ቋንቋ የተተረጎመ)

ለወንድም አላሞ፥

በክርስቶስ ውድ ወንድማችን፥ ገጸ ድርህን በጣም ወድጄዋለው፥ ከመግለጫዎችህም ጋር ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን ጨምረን ጨማምረን በጥብቅ የምናጠናበት ጊዜ ነው ብየ አምናለው።

እባክህ 33 ትንቢቶች ያሉትን መሲሁ የተባለውን መጽሐፍ የምትችል ከሆነ እንድትልክልኝ እለምና ለው። በተጨማሪም፥ በነዚህ ወሳኝ በሆኑ ርዕሶች ላይ ሌላ ቪድዮ ወይም መጽሐፍ ካለህ እባክህ ላክልኝ።

በጣም አመሰግናለሁ እንዲሁም እነዚህን እውነታ ዎችን እንድትናገር ላንተ አገልግሎት እጸልያለሁ።

በረከት በክርስቶስ፥

ቤኤትሪዝ ማርቲኔዝ

ፊርንትሪ ገሊ፥ ቪክቶርያ፥ አውስትራሊያ

## ኒው ሜክሲኮ

ከብዙ አመታት በፊት ፒተር ኸርናንደዝ በአእምሮ ውስጥ በነበረ ቱመር (እብጠት) በጣም ታሞ በእስር ቤት ውስጥ ነበር። ዶክተሮች ለመኖር 90 ቀናት እንደ ነበሩት ነገሩት። እርሱም ወደ ፓስተር አላሞ ጻፈለት: ደብዳቤው እምነቱን በማበርታት እና እጁን በመዘርጋት ፈውሱን እንዲያውጅ አበረታታው። ቤተ ክርስትያንዋ በሙሉ ለእርሱ ጸለየችለት። ፒተር የምስጋና ደብዳቤ መልሶ ጻፈ፥ ምክንያቱም ጌታ ፓስተር አላሞን በታላቅ መንገድ ተጠቅሞት ተፈወስኩ በማለት። ፒተር በድል መጓዙን ቀጥሏል፥ የጎልፍ ኳስ መጠን የነበረው የአእ ምሮ ቱመር (እብጠት) ተጽእኖ ሳይፈጥርበት። ጌታ መቶ ፐርሰንት ፈወሰው፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተፈትቶ ከሚስቱ እና ከሴት ልጁ ጋር አብሮ መሆን ቻለ።

በቅርቡ በላስ ክሩሴስ፥ ኒው ሜክሲኮ የወንጌል ጽሁፍ ሲያከፋፍሉ የነበሩ የቤተ ክርስቲያንዋ ጥንዶች በአጋጣሚ አገኙት። ፓስተር አላሞ በችግር ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ሁልጊዜ ይረዳ እንደነበረ እንደሚያስታ ውስ፥ በእስር በነበረ ጊዜ ልብስ በመላክ፥ በቤተ ክር ስቲያን ውስጥ የመኖርያ ስፍራ በመስጠት የእርሱን ቤተሰብ እንደረዳ ነገራቸው። ቶኒ በችግሩ ሰዓት እን ደረዳው ፒተር ተናግሯል።ፒተር ቶኒን እና ቤተ ክር ስትያንን በህግ ስራው ሊያገለግል እንደሚፈልግ እና በእርሱ አከባቢ የወንጌል ጽሁፎችን ሊያከፋፍል እንደ ሚፈልግ ተናግሯል።

## ዩናይትድ ኪንግደም

ወንድሜ ቶኒ ሲናገር ቫቲካን በፍርሀት መንቀጥቀጥ ይጀምራሉ። ወንድሜ ቶኒ፥ ሰይጣን በሽሽት ላይ እንዲሆን አድርገሃል፥ በኢየሱስ ስም፥ አሜን።

ጆናታን ቤሊ — ኒውካስል፥ ዩናይትድ ኪንግደም

# በደህንነት እና በሃይማኖት መካከል ያለ ልዩነት

(ከገጽ 5 የቀጠለ)

መሆን ትፈልጋለህ? ምርጫህ የክርስቶስ አካል መሆን ከሆነ ይህን ጸሎት ጸልይ፡-

ጌታዬ እና አምላኬ፥ ለነፍሴ ምህረት አድርግላት፥ ሃጥያተኛዋን።[21] ኢየሱስ ክርስቶስ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ።[22] በመስቀል ላይ እንደሞተ እና ክቡር ደሙን ለቀድሞ ሃጥያቶቼ ስርየት እንዳፈሰሰ አምናለሁ።[23] እግዚአብሔር ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ከሞት እንዳስነሳው[24] እና በአሁኑ ሰአት በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ የሃጥያቴን ኑዛዜ እና ይህን ጸሎት እንደሚሰማ አምናለሁ። የ[25] ልቤን በር ከፍቼ ወደ ልቤ እጋብዝሃለው፥ ጌታ ኢየሱስ።[26] እርኩስ ሃጥያቶቼን በሙሉ በእኔ ቦታ በመሆን በቀራንዮም ባፈሰስከው በክቡር ደምህ እጠብልኝ።[27] አትመልሰኝም፥ ጌታ እየሱስ፤ ሃጥያቶቼን ይቅር ትልና ነብሴን ታድናለህ። ቃልህ፥ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ይህን ስለሚል አውቃለሁ።[28] ቃልህ ማንንም እንደማትመልስ ይናገራል ያ ደግሞ እኔንም ያጠቃልላል።29 ስለዚህ፥ እንደሰማኸኝ አውቃለሁ፥ እንደመለስክልኝ አውቃለሁ እና እንደዳንኩ አውቃለሁ።30 እና አመሰግንሃለሁ፥ ጌታ እየሱስ፥ ነብሴን ስለአዳንክ፥ ምስጋናየን ያዘዝከውን በማድረግ እና ሃጥያትን ባለመስራት አሳይሃለሁ።[31]

በመንፈስ ቅዱስ አልፎ ክርስቶስ እና እግዚአብሄር በአንተ ዉስጥ ይኖራሉ፡፡ ሙሉ የሆነዉን የእግዚአብሄር መለኮታዊ ባህሪን በአንተ ዉስጥ ልትቀበል የምትችልበት መንገድ አለ፡፡ የእግዚአብሄር መለኮታዊ ባህሪ በአንተ ዉስጥ በብዛት ሲኖር፣ በሚሊዬን የሚቆጠሩ ብዙሃን ክርስቲያኖችን በቀላሉ ከደኅንነት ያወጣቸውን ፈተናዎች የመቋቋም ብቃት ይኖርሃል። ለጥምቀቱ በቅዱስ መንፈስ ውስጥ ጸልዩ፡፡ በቅዱስ መንፈስ ውስጥ ጥምቀትን እንዴት መቀበለ እንደሚቻል እና በይበልጥ የእግዚአብሄር መለኮታዊ ባህሪ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ለማወቅ፤ በእኛ የተዘጋጀዉን ጽሁፍ ይጠይቁ ወይም ይደዉሉልን፡፡ ያለ ቅድስና እግዚአብሄርን ሊያይ የሚችል የለም እና (ወደ እብራዊያን 12፥14)

ከመዳን በኋላ፥ ኢየሱስ ተጠመቁ ይላል፥ ውሃ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በመግባት፥ በአብ፥ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም።[32] መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት አጥኑ እና የሚለውን አድርጉ።[33] ይህ ለእናንተም ሆነ ለሌሎች ይጠቅማል።

ሰለመዳናችሁ ለሌሎች እንድትናገሩ ጌታ ይፈልጋል። የፓስተር ቶኒ አላሞ የወንጌል ጽሑፍ አከፋፋይ መሆን ትችላላችሁ። ጽሑፍ በነጻ እንልክላችኋለን። ለተጨማሪ መረጃ ይጻፉልን ወይም ይደውሉልን። ይህን መልእክት ለሌላ ሰው ያስተላልፉ።

አለም ሁሉ እንድትድን ከፈለጋችሁ፥ ኢየሱስ እንደሚያዘው፥ እግዚአብሔርን በአስራት እና በመባ አትስረቁት። እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፥ “ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በኵራት ነው።እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ [ይህ አለም ሁሉ]፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ። በቤቴ ውስጥ [የዳኑ ነፍሳት] መብል [የመንፈሳዊ መብል] እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ [አሥራት የ10% ከጠቅላላ ገቢ ነው] ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ስለ እናንተ ነቀዙን እገሥጻለሁ፥ የምድራችሁንም ፍሬ አያጠፋም፤ በእርሻችሁም ያለው ወይን ፍሬውን አያረግፍም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።የተድላ ምድር ትሆናላችሁና አሕዛብ ሁሉ ብፁዓን ብለው ይጠሩአችኋል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር” (ሚል. 3፥8-12)።

**21** መዝ. 51:5፣ ሮሜ 3:10-12፣ 23 **22** ማቴ. 26:63-64፣ 27:54፣ ሉቃ. 1:30-33፣ ዮሐ. 9:35-37፣ ሮሜ 1:3-4 **23** ሐዋ. 4:12፣ 20:28፣ ሮሜ 3:25፣ 1ኛ ዮሐ. 1:7፣ ራዕ.5:9 **24** መዝ. 16:9-10፣ ማቴ. 28:5-7፣ ማር. 16:9፣ 12፣ 14፣ ዮሐ. 2:19፣ 21፣ 10:17-18፣ 11:25፣ ሐዋ. 2:24፣ 3:15፣ ሮሜ 8:11፣ 1ኛ ቆሮ. 15:3-7 **25** ሉቃ. 22:69፣ ሐዋ. 2:25-36፣ ዕብ. 10:12-13 **26** 1ኛ ቆሮ. 3:16፣ ራዕ. 3:20 **27** ኤፌ. 2:13-22፣ ዕብ. 9:22፣ 13:12፣ 20-21፣1ኛ ዮሐ.1:7፣ራዕ. 1:5፣ 7:14 **28** ማቴ. 26:28፣ ሐዋ. 2:21፣ 4:12፣ ኤፌ. 1:7፣ ቆላ. 1:14 **29** ማቴ. 21:22፣ ዮሐ. 6:35፣ 37-40፣ ሮሜ 10:13 **30** ዕብ. 11:6 **31** ዮሐ. 5:14፣ 8:11፣ ሮሜ 6:4፣ 1ኛ ቆሮ. 15:10፣ ራዕ. 7:14፣ 22:14 **32** ማቴ. 28:18-20፣ ዮሐ. 3:5፣ ሐዋ. 2:38፣ 19:3-5 **33** ዘዳ. 4:29፣ 13:4፣ 26:16፣ ኢያ. 1:8፣ 22:5፣ 2ኛ ጢሞ. 2:15፣ 3:14-17፣ ያዕ. 1:22-25፣ ራዕ. 3:18

ለበለጠ መረጃ ወይም ሌላ ርእስ ላይ የተጻፉ ሊፈልጉዋቸው የሚችልዋቸው ጽሑፎችን እባክዎ ያግኙን።

**Tony Alamo, World Pastor, Tony Alamo Christian Ministries Worldwide • P.O. Box 2948, Hollywood, CA 90078**

**የ24 ሰአት የጸሎት እና የመረጃ መስመር፡- (661) 252-5686 • ፋክስ (661) 252-4362**

**www.alamoministries.com • taoffice@alamoministries.com**

*የቶኒ አላሞ አለምአቀፍ አገልግሎቶች ለህይወት የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ያሉበትን የመኖርያ ስፍራ አዘግጅቷል፥ በዩ.ኤስ. ባሉን ስፍራዎች ጌታን በሙሉ ልባችሁ፥ ነፍሳችሁ ሀሳባችሁ እና ሀይላችሁ ልታገለግሉ ለምትፈልጉ ሁሉ*

**በኒውዮርክ ሲቲ አገልግሎቶች ሁሌ ማክሰኛ 8 ፒ.ኤም. እና በምሽት በሌሎች ስፍራዎች ይካሄዳሉ እባክዎ ለበለጠ መረጃ በ (908) 937-5723 ይደውሉ። ምግብ ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ ይኖራል።**

**የፓስተር አላሞን መጽሐፍ ይጠይቁ፡- መሲሁ፥ ክርስቶስን በብሉይ ኪዳን ከ333 በላይ በሆኑ ትንቢቶች ማሳየት።**

*በነፍሳት መከር ውስጥ የፓስተር አላሞ ጽሑፎችን በማከፋፈል ሰራተኛ ይሁኑ።*

*ሁሉም የጹሁፍ እና የድምጽ መልእክቶቻችን ነጻ ናቸው፥ መጓጓዣን ጨምሮ።*

*ገንዘብ ለእነዚህ ሊያስከፍሏችሁ ቢሞክሩ በ(661) 252-5686 ይደውሉ (ለመደወል ነጻ ነው)።.*

**ይህ ጹሁፍ እውነተኛውን የደህንነት እቅድ ይዟል (ሐዋ. 4፥12)።**

**አይጣሉት፥ ለሌላ ሰው ይስጡ።**

**በሌሎች ሃገራት ላላችሁ፥ ይህን ጽሑፍ ወደ ራሳችሁ ቋንቋ እንዲተረጎም እናበረታታለን። መልሰው ካሳተሙ፥ እባክዎ ይህን ያጠቃሉ፡-**

© የቅጅ መብት ኤፕርል 2013, 2015 ሁሉ መብት የተጠበቀ ወርልድ ፖስተር ቶኒ አላሞ ® የተመዘገበው ኤፕርል 2013, 2015

AMHARIC—VOLUME 17800—*THE DIFFERENCE BETWEEN SALVATION AND RELIGION*